# አንጋፋው ጋዜጠኛ ፀጋዬ እንደሻው

በዚህ የዲያስፖራ ሕይወቴ የቅርብ ወዳጆቼንና ጓደኞቼን በሚመለከት አስደሳችም አሳዛኝም ገጠመኞችን አስተናግጃለሁ። እንደ ባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ሃሳብን በነጻ የመግለጽ ነጻነት ዓለም አቀፍ ሽልማት (Freedom of Expretion International Award, 2005) አሸናፊነቱ ያስደሰተኝን ያህል፣ የጋሼ ድንገተኛ ሕልፈትና ቀደም ሲልም የጓዴ የተፈራ አስማረ አሳዛኝ አሟሟት ትልቁን ስፍራ ይይዛል። አሁን ደሞ የጓዴ የወንድሜና የርኾም ዘመን የሥራ ባልደረባዬ የነበረው ያንጋፋው ጋዜጠኛ ፀጋዬ እንደሻው ሕልፈት ሌላው ክፉ አጋጣሚዬ ነው። ፀጋዬ ጳጉሜን 5 ቀን 2000 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።



ፀጋዬ እንደሻው



ተፈራ አስማረ

አንጋፋው ጋዜጠኛ ፀጋዬ እንደሻው የሲዳሞ ልጅ ነው። አገረ ማርያም በ1935 ተወልዶ፣ እዚያና ይርጋ ዓለም የደገ። በኋላም የ2ተኛ ደረጃ ትምህርቱን በዝነኛው የንግድ ሥራ ሙያ ትምህርት ቤት የተማረ። በጽሕፈት አያያዝ የሙያ መስክ ሠልጥኖም በዘመኑ የነበረው የኢምፔሪያል አንሹራንስ ኩባንያ ባልደረባ በመሆን የሥራ ዓለምን ሀሁ… መቁጠር የጀመረበት። በዚያን ዘመን አጠራር ዜንጦ ከሚባሉ አሮው ነች ሸሚዝ ለባሾች፥ ባለከፍታ ተረከዝ አፍንጫ ሹል የቴክሳሶች ጫማ አዘውታሪዎችናና ግልጥ አውቶሞቢል አሽከርካሪ ያራዳ ልጆች ጎራ የተሰለፈ ነበር። ለያኔው ጸጋዬ ሽቅርቅርነት የሚወረወሩት ያድናቆት እይታ ዐይኖች መንገድና ቤት ይቁጠረውየሚሰኙ  ብቻ ነበሩ።

EthioLion.Com

የኋላ ኋላ ፀጋዬ ኢምፔሪያል ኢንሹራስን ለቆ በቀጥታ ያመራው ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ነበር። በማስታወቂያ ሚኒስቴርም የሬዲዮ መምሪያ ዳይሬክተር የነበሩት የክቡር አቶ ንጉሤ ሀብተ ወልድ (“ዲግ ታይገር” በሚል ቅጽል ቁመናቸውንና ባሕሪያቸውን አመዛዝነው ሠራተኞቻቸው ይጠሩዋቸው የነበሩት ባለሥልጣን) ልዩ ጸሐፊ ሆኖ ነበር… የተቀጠረው። እያደር ካየሩም ከሰዉም እየተላመደ ሲሄድ፣ ከዘመኑ ዝነኛ ጋዜጠኞች ከነአሳምነው ገብረ ወልድ፥ ሰሎሞን በቀለ፥ ተክሉ ታቦር፥ ታደሰ ሙሉነህ ወዘተ… የማግባቢያ ጥያቄ ይጎርፍለት ገባ። “ድምጽህ ለሬዲዮና ለቲቪ ሚዲያ የሚስማማ ስለሆነ እባክህ ጋዜጠኝነቱን ሞክረው….” የሚል ውትወታ ነበር። አዎን…. ፀጋዬ ለጥሪው ገበረ። የቢሮክራሲውን ቢሮ ለቆ እስቱዲዮ ገባ። ተወዳጅነትን ባጭር ጊዜ ካድማጮቹ ሲያገኝ፣ የነጻ ትምህርት እድልም ወዲያው መጣለት። እናም ጀርመን አገር ሄዶ በድምጽ መገኛኛ ሙያ ጋዜጠኝነት ላንድ ዓመት ተመንፈቅ ያህል ሠለጠነ። ሁሌም ወደሚያበረቃት እናት አገሩ ተምልሶ፣ የሬዲዮ ጋዜጠኝነት ሕይወቱን ቀጠለ።

ባብዮቱ ጅማሮ ዓመታት ላይም እኔ፥ ተፈሪ አስማረ፥ ሙሉጌታ ወልደ ሚካዔል፥ ንጉሴ አክሊሉ፥ ላእከ ማርያም ደምሴ ወዘተ… ተቀላቀልነው። ፀጋዬን ተዋወቅነው። ቤቱን አላመደን፥ ደግ ልቡን ሰጠን፥ ያንን የማያልቅበትን ቀልዱንና ቁመነገረኛነቱን አስኮመኮመን። ሰው ሲቸገር ኪስን አራግፎ፣ የእለት ጉርስ ለራስ ማጣትን ወዘተ… ወዘተ… ፀጋዬ አስተማረን። የሚያሳዝን ነገር ሲገጥመው፣ እፍኝ ሙሉ እምባውን ያለገደብ ማዝነብ መቻሉን በርሁርህ ተፈጥሮው አሳየን። በዚያው ልክ በተላላነቱና በየዋህነቱ አንድያ ብቸኛ አንዲት ክፍል ቤቱን በጮሌዎች ተነጥቆ ኖረ። በዚህና በጨካኞቹ የማስታወቂያ ሚኒስቴር የደርግ ታማኝ ትክለኞች፣ ለበረንዳ አዳሪነት እስከመታጨትም ደረሰ።

አምበሳው ፀጋዬ፣ “የጀግናውን ጦራችንን የመጨረሻ የድል ምእራፍ አብሬ ሳልጨብጥ ከጦር ግምባር አልመለስም” ብሎ በ1971 ዓ.ም. ለስድስት ወራት በኤርትራ በረሃ ሲንከራተት ቆይቶ ቆስሎ ሲመለስ፣ የጠበቀው ምስጋና ወይ ሽልማት አልነበረም። ይልቅስ ከሥራ መባረር ነበርና የገንጣይ አስገንጣይ ቤተኞቹ የቅርብ አለቆቻችን እነ ገዳሙ አብርሃ (በኋላ ክዶ ከዘመዶቹ ጎራ የተቀላቀለው) ቁጭታቸውን በደካማው ፀጋዬ እንደሻው ላይ ተወጡ። (ከሱ ቀደም ሲል ይህን መሰሉን እጣፈንታ የቀመስነው በዚህን ጊዜ የኢትዮጵያን ሬዲዮ ግምኛ (forbad) ተሰናብተን ወጥተን ነበር።) ፀጉ ወር ተራው ደርሶ ሕይወቱ ወደማይመለስበት መቀመቅ ውስጥ ወረደ። ሥራ አጥ ሆነ። መጠለያውን ተሸለተ። እናም አለው አለውና ሲደክመው ወደ ገጠር ገባ። ለብዙ ዓመታት ድምጹ ጠፍቶ ቆይቶ፣ ደጋጎቹ የማስታወቂያ ሚኒስቴር አለቆቻችን እኛን የጠፋነውን በጎቻቸውን ለክፉ ቀናቸው ማፈላለግ ጀመሩ።

በ1980 ዓ.ም. ፀጋዬን ባሌ ክፍለ ሀገር አጋርፋ የገበሬዎች ማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ አግኝተው እያዳፉ ወደ ሰሜን ጦር ግምባር ላኩት። እኔን ከሕዝብ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን መንጥቀው ታጠቅ ሰደዱኝ። “ምነው?” አልን። “በጦር ግምባር የመገዘጥም፥ የመታገልም፥ የመቁሰልም፥ የመሞትም… ልምድ ስላላችሁ በጣም ትፈለጋላችሁ” አሉን እነ መጋቢ ያምሳ አለቃ ለገሰ አስፋው። ስውር ደባቸውና ሸራቸው ባሰኒ ላገራችንስ መቆማቸን ያለ የነበረና ወደፊትም የሚኖር በመሆኑ፣ ለእምዬ ስንል ዳግም ዘመትንላት። ብዙ ብዙ ትዝብትም ይዘን ተመለስን… በ1970 እና 71 ዓ.ም. የነበረው የጦሩ የተዋጊነት ሞራል ወድቆ፤ አዛገሮች (በተለይም



EthioLion.Com

አብዛኛውን ሕይወታቸውን በጦር ግምባር ያሳለፉ) በመጨረሻዋ ሰዓት ላይ ለልጆቻቸው መጠለያ ሊያቆሙ ባዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የከተማ ልማትን ቢሮዎች ደጅ ሲጠኑ የተስተዋሉበት አሳዛኝ ፍጻሜ ነበር። የደርግም መጨረሻ ብዙ ሳይቆይ ያየነውን ሆነ።

ጸጋዬ እንደሻው የሚታውስባቸው ብዙ ሙያዊ ገድልና ባሕሪያትም ነበሩት፡፤ ለቡዙዎቹ የያኔው ዘመንተኞች እንደሚታወሰው፣ ፀጋዬ እንደሻውና ተፈራ አሥማረ ድምጽ ማጉያ እየተቀባበሉ ባብዮት አደባባይ ይካሄድ ለነበሩ ሰልፎች የቀጥታ ሬዲዮ ስርጭት ተግባር ያከናውኑ እንደነበር አይዘነጋም። ፀጋዬ ከበድ ከበድ ያሉ የመስክ ዘገባዎችን በመላው አገሪቱ እየተዘዋወረ በመዘገብ ሬዲዮ ጣቢያውን ሕይወት ከሚዘሩበት ብርቱ ጋዜጠኞች አንዱ ነበር። ከሥራ ባደረቦቹም ጋር ይሁን ከምንኛውም የሰው ልጅ ጋር ባጭር ጊዜ ውስጥ ተግባብቶ ተዝቆ የማይልቀውን ለዛ ያለውን ቀልዱን የሚመግብ ደግ ሰው ነበር፡፤ ፀጋዬ የሸርና የተንኮልን ክፉ ባህሪነት የማያውቅ ግልጽነት፥ ደፋርነትና ሀቀኝነትና ምርኩዝ መሰላሉ አድርጎ የኖረ የመንፈስ ባለጸጋ ነበር።

ፀጋዬ እንዳንዳንዶቻችን ሁሉ ወደ ሰሜን ጦር ግምባር ዘምተው ከነበሩና ከቆሰሉ ጋዜጠኞች አንዱ ነበር። የዚያ የዘማች ጋዜጠኝነቱ ጦስ፣ በሥልጣን ላይ በነበሩ (በማስታወቂያ ሚኒስቴር) የገንጣይ አስገንጣይ ምንደኛ አለቆቻችን ለበረንዳ አዳሪነት ችግር እስከመጋለጥ ደርሶ እንደነበር እስከዛሬም በሃዘን እናስታውሰዋለን። በመጨረሻም የማስታወቂያ ሚኒስቴር ጋዜጠኝነት ህይወቱ በዚሁ አክትሞ ወደ ገጠር ተሰዶ መውጣቱ ይታወሳል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት የጀርመን ድምጽ ራዲዮ ወኪል በመሆን ካዋሳ ከተማ መልካም ዜናዎችን ሲያስተላልፍ ቆይቷል። ባለፈው ታህሳስ ወር አገር ቤት በነበርኩበት ወቅት፣ አዋሳ ድረስ ሂጄ ስጠይቀው፥ ጤናው አስጊ ሁኔታ ላይ እንደነበር ለማሰተዋል አላዳገተኝም። እናም ያንን ደግና ለወገኖቹ ሁሌም ደራሽና ተቆርቋሪ ወንድም ጓድ በሞት በማጣቴ ሃዘኔ ብርቱ ነው። ያ ሀቀኝነቱ ለኔ ብጤው ስሱ ፍጡር ብዙ ያጎላል። ምስክር ይነሳል፣ እማኝ ይነጥቃል። ትናንት ጓዴን አብሮ አደጌን ተፈራ አስማረን በምቀኞች የዲያስፖራ ሴረኞች ኔዘርላንድ ላይ አጣሁት። ከዚያም ጋሼ ፀጋዬ ገብረ መድህንን.... ዛሬ ደሞ ሆደ ቡቡውን የዋሁን ጸጋዬ እንደሻውን ተለየሁት። ያንን ያዛኝ እፍኝ ሙሉ እምባውን ከንግዲህ ወዲህ አናይም።

ልዑል እግዚአብሄር የፀግዬን ነፍስ ከመንበሩ አይለየው። ለቤተሰቡ፥ ለሥራ ባልደረቦቹና ለጋራ ጓደኞቻችን ሁሉ መፅናናትን እመኛለሁ።

- አበራ ለማ (ኖርዌይ)

<u>አባሪ</u>

**ከቀንም ቀን አለ** (ለፀጋዬ እንደሻው የዘመኑ እንግልት መታሰቢያ፣ **ሽበት**…
በአበራ ለማ፣1972)

EthioLion.Com

EthioLion

# ከቀንም ቀን አለ!

አዎን ከቀንም ቀን አለ!
ደስ የሚል አንቁጣጣሽ የመሰለ...
የሚበረቃ የሚጊጊ ሰዓት በሰኮንድ የሚለካ
ብርቅዬ እንዳያልቅ የሚጠሩት የሚጨንቁት
ከቀንም ቀን አለ! እንደዛሬው
ብዙ ትዝታ የሚያጠቃው
ባንዱ ሲደሰት ባንዱ ሲያኮርፍ
የኔ ቢጤን የሚያከንፈው

ከቀንም ቀን አለ! የማይረሳ
በየደቂቃው በጆሮግንድ የሚያገሳ
"ነበር..." የሚያሰኝ ላፍታ
ለቃል ቢዳን ለውለታ
ከቀንም ቀን አለ! ባንዳንድ ምሽት
ለስለስ ያለ ዜማ የሚፈስበት
ቤተኛው ሁሉ የሚስቅበት የሚያወካበት
በሳሎን ምላሽ የሚያዜምበት

ከቀንም ቀን አለ! ያልተወለደ
ገና በነግህ የተጠመደ



Ethiopia Will Prevail!

EthioLion

“ምኑን ዓይተህ ...” የሚሰኙበት
የሕይወት ትርጉም የሚያነሡበት
ለቀንም ቀን አለ/የማይረሱት
እንደ እሳት ጡት የሚናፍቋት
እንጎቻ ሆኖ የማይበሉት
“ነበርኩኝ! ...” ብለው የሚሸፉት
ወጥተው ወርደው፣ የማያገኙት የማያዩት የማይዳስሱት
ለቀንም ቀን አለ! ታጋይ ተመርሮ የዋለበት

ሰፀጋዬ እንደሻው
፲፱፻፸፪



Ethiopia Will Prevail!